# ጅላጅሉ ተንታኝ ገመቹ

ዘውዲቱ የማነ

2019-10-08

አንትሮፖሎጅስት ተብለው ምርምርና ጥናት ያደረጉ የተባሉት ዶክተር ገመቹ መገርሳ ቀደም ሲል መለስ ዜናዊን ብዙ ፕሮፌሰር ቢሰበሰብ መለስን አይወዳደርም ብለው ለመተዳደር ሲሉ በአድርባይነት  ሲያሞካሹ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው።

ሰውየው በምርጫ 97 ግድያ፣ አጣሪ ኮሚቴ ሆነው ከመንግስት የወገኑ ግብዝ ሰው ዛሬ ደግሞ ተረኛና ነውረኛ ከሆኑት የኦሮሞ ልሂቃን አንዱ ሆነው ቀርበው የሚከተለውን ይላሉ። ክርስትና የተነሳ ኦሮሞ ሁሉ አማራ ነው። እስልምናም የአማራ ባህል ስለሆነ እስላሙ ሁሉ አማራ ነው ብለው አስደምመውኛል። ቢያንስ በኦርቶዶክስ የጅምላ የክርስትና ስም አወጣጥ ስለሌለ ሰውየው እንደምሁር ሳይሆን ሀላፊነት በጎደለው ሁኔታ ትንታኔ ሲሰጡ የበታችነት ስሜት ተጠቂ፣ የሀሰትና የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ በመንዛት የተካኑ ይመስላሉ። ዶክተሩ አራዳ የሚለውን ቃል ሲተነትኑ ሌባ ወሮበላ ቀጣፊ ነውም ብለዋል።https://www.youtube.com/watch?v=4WO4W4cABfs

ሰውየው በሀሰት የታሸገ ጨለምተኛና የጥላቻ ትርክት በአማራና በክርስትና ላይ ሲነዙ የመጀመሪያቸው አይደለም። https://www.youtube.com/watch?v=zXi1LIUk5dw&t=165s

ወደጉዳየ ስመለስ ዶክተር ገመቹ መገርሳ ባነጋገር ብዙ የተሳሳቱት ነገር ቢኖርም የእኔ ትኩረት ያረፈው ግን የኦሮሞ ክርስቲያንና እስላም አማራ ከሆነ ለእሳቸው ኦሮሞ ማን ሊሆን ነው? ዶክተሩ ያሉትን ከተቀበልን፣ በክርስትናና በእስልምና እምነት ውስጥ ያሉ አማኞች ሁሉ፣ ዘመነኛው የጎሳ ክፍፍል የማይበግረው፣ አምላኩ በሰማይ የሚኖር ዜጋ ስለሆነ የጥላቻና የመከፋፈል ትርክቱን ንቆ ከመተው ሌላ አማራጭ አይኖረውም።

ጅ ላጅል ገመቹ ምሁር ይባላሉ

ል ጅ አያስበውም የሚያስቡት ሁሉ

አ ማራ ነው አሉ ክርስቲያን በሙሉ

ይ ገርማል እስላምም አማራ ነው አሉ

ሙ ሉ ትኩረታቸው ቢሆንም ጥላቻ

ት ንሽ መንፈሳቸው አያገኝም አቻ

እ ንዳሉት ብናስብ ይሁን ብንላቸው

ን ገሩኝ ገመቹ ምን ይሆን ትርፋቸው?

ዲ ያቢሎስ ሀሳብ ምሁር ካሰኛቸው

ያ ስያዙንን ቀመር እንቀበላቸው

ጫ ጫታ ያቁሙ ሰው ማደናገር

ው ጤቱ ይሰላ አማኝ ይቆጠር

ት ልቁ ዜጋችን በአንድነት ይኑር።